## የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ የሁለተኛ ሩብ አመት የስራ አፈጻጸምን የያዘ መረጃ ፍኖተ-ልማት ዜና-መጽሄት

### መግቢያ

አገራችንን በ2022 ኢትዮጲያ "የአፍሪካዊት የብልጽግና ተምሳሌት" ለማድረግ ሀገራዊ የአስር ዓመት መሪ ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡

የከተማ ልማት ስራም ባለ ብዙ ዘርፍ እንቅስቃሴዎችን ያካተተ ሲሆን ይህም የኢንዱስትሪ፣ የገበያ፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መሰረተ-ልማት አገልግሎቶችን በቅንጅትና በተመጋጋቢነት በውስጥም ሆነ ከአካባቢው ጋር ትስስር በመፍጠር መምራት የሚጠይቅ ነው፡፡ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ስራችንም ከግብርና ቀጥሎ ሰፊ የሥራ እድል የሚፈጠርበትና የሀገራችን የኢንዱስትሪ መሰረትና ሁለንተናዊ ዕድገት የሚወስን ስትራቴጅክ ዘርፍ ነው፡፡ በመሆኑም ሁሉም የልማት ስራዎች ምን አይነት አላማና ግብ ይዘው ከስራ ዘርፋቸው አቅጣጫ በተጨማሪ ወደ ጋራ ውጤትና የተቀናጀ የልማት አቅጣጫ እንዲያመሩ በማስፈለጉ ይህንን አቅጣጫ የያዘ የከተማ ልማትና የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች እንዲሁም ወደ ተግባር የሚያስገቡ የልማትና መልካም አስተዳደር ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ከዞኖችና ከከተማ አስተዳደሮች የተናበበ ዕቅድ እንዲኖረን በማድረግ ሲሰራ ቆይቷል፡፡

በዚህም መሰረት የ10 ዓመት መሪ ዕቅድ፣ የ5 አምስት ዓመት ስትራቴጅክ ዕቅድና የ2013 በጀት አመት እቅድ አዘጋጅቶ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡ በመሆኑም በ2013 በጀት አመት በሁለተኛ ሩብ አመት የተሰሩ ክንውኖችን የቢሮው ማናጅመንት ኮሚቴው ገምግመዋል፡፡ በግምገማው ላይም በሁለተኛ ሩብ አመት ላይ ታቅዶ ያልተከናወኑ ክንውኖች በቀጣዩ ሩብ አመት ላይ ትኩረት ተሰጥቶ መሰራት እንዳለበት አጽንኦት ሰጥተዋል፡፡ ከዚህም መነሻ የ2013 በጀት አመት የሁለተኛውን ሩብ ዓመት ዕቅድ የስራ አፈጻጸምን በተመለከተ በየሩብ አመቱ እየተዘጋጀ በሚወጣው ፍኖተ-ልማት ዜና-መጽሄታችን ላይ እንደሚከተለው አቅርበናል፡፡

### በዝግጅት ምዕራፍ የተከናወኑ ተግባራት ስንመለከት፡-

በዝግጅት ምዕራፍ የሁለተኛውን ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ማጠቃለያ ጊዜ እንደመሆኑ በርካታ ስራዎች የተሰሩ ቢሆንም በዋናነት የ10 ዓመት መሪ ዕቅድና በ5 ዓመት ስትራቴጅክ ዕቅድ በማዘጋጀትና በየደረጃው ውይይት ተደርጎበት ከፀደቀ በኃላ የተቀመጡ ግቦች፣ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችንና የአፈጻጸም አቅጣጫዎችን እንደ መነሻ ሁኔታ በመጠቀም የበጀት ዓመቱ ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡

የተዘጋጀውን ዕቅድ ፈጻሚ ከማዘጋጀት ረገድ በቢሮ ደረጃ ሁሉም ፈጻሚዎችና ዳይሬክቶሬቶች ከስራ ክፍሉ ሰራተኞች ጋር በዕቅዱ ዙሪያ እንዲወያዩ ከተደረገ በኃላ በቢሮ ማናጅመንት ከጸደቀ በኃላ ሁሉም የቢሮ አመራርና የተለዩ ባለሙያዎች በተገኙበት ለ1 ቀን በቆየ የውይይት መድረክ በማዘጋጀት የ2012 በጀት ዓመት እቅድ የቀጣይ ትኩረት አቅጣጫ ዙሪያ የተቋሙ ሠራተኞች ጋር ውይይት በማድረግ መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡

እንዲሁም የሴክተሩን የ2013 ዕቅድ በውጤት ተኮር ስርዓት መሠረት በማዘጋጀት ከዳይሬክቶሬቶች ጋር ለመፈራረምና ለፈጻሚዎች በማውረድና እንዲተገብሩት መግባባት ላይ ለመድረስ እየተሳራ ሲሆን ወደ ዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች የማውረድና የመፈራረም ስራም በዚሁ መልኩ በመስራት ተቋማቱ ዕቅዱን በየደረጃው የማውረድ ስራ እንዲሠሩ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ወደ ትግበራ ለመግባት ተችሏል፡፡

### የግቦች አፈጻጸም ሪፖርት ስንመለከት፡-

## የተገልጋዮችን ዕርካታ ከማሳደግ አንጻር፡-

- የተገልጋዩን ዕርካታና አመኔታ ለማሳደግ ወደ ተቋሙ የሚመጡትን አቤቱታና ቅሬታዎችን መፍትሔ መስጠት ጋር ተያይዞ ወደ ተቋሙ ከሚመጡ አቤቱታዎች መካከል 60% ምላሽ በመስጠት ከፈርጅ ሁለት እስከ አምስት የሚገኙ ከተሞች በማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አቅርቦት የነዋሪው ዕርካታ ደረጃ በመመዘን 60 በመቶ መድረሱን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
- 5 የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች በስራ ቦታ ላይ የሠራተኞችን ደህንነት መጠበቂያ አልባሳትና መሳሪያ እንዲያሟሉ ተደርጓል፡፡
- በሴክተሩ በሚከናወኑ ስራዎች የሴቶች፣ የወጣቶችና ልዩ ድጋፍ የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን ከማረጋገጥ አኳያ የሴቶችና ወጣቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት 18.5 በመቶ መሆኑ እና የሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት 12.5 መቶ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
- የ5 ዓመት ስትራቴጅክ ዕቅድና የ2013 በጀት ዓመት የሴክቴር ዕቅድ በማዘጋጀት የመናበብ ስራ የተሰራ ሲሆን የ2013 በጀት ዓመት ዕቅድ ከ7 የታችኛው ተቋም ጋር መፈራረም ተችሏል፡፡
- 1 (100%) ጊዜ የዘርፉን የፊዚካል ዕቅድ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ በማድረግ 2 (100%) ተቋማዊ ሪፖርት በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት ተልኳል፡፡ በተጨማሪም በተቋሙ አጠቃላይ የስራ ክንውኖችና ተልዕኮ አፈጻጸም ዙሪያ በህትመትና ኤሌክትሮኒክ ሚዲያ መረጃዎችን ለህብረተሰቡ 1 (100%) ጊዜ ተደራሽ ተደርጓል፡፡

## የከተሞች የፋይናንስ አስተዳደር አቅምን ማሳደግን በተመለከተ፡-

- በከተሞች የገቢ አሰባሰብ የህግ ማዕቀፎችን መሰረት በማድረግና ለ1 ከተማ ማለትም ለአሶሳ ከተማ የገቢ ማሳደጊያ እቅድ (REP) በማዘጋጀት 0.053 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡
- በክልሉ ያሉ ሁሉም ቁጠባ ቤቶች ላይ 287,290 ብር ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡
- በተሻሻለዉ የገቢ ታሪፍ መሠረት ከተሞች ገቢ መሠብሠባቸዉን በተመለከተ በ6 ከተሞች ክትትል በማድረግ 1 ጊዜ ግብረ-መልስ ለመስጠት ተችሏል፡፡
- የህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄ ስራዎች አተገባበርን በተመለከተ በግማሽ ዓመቱ በ1 ከተማ የአካል ድጋፍ በማድረግ 1 ጊዜ ግብረ-መልስ ለመስጠት ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት ክትትል በማድረግ ግብረ-መልስ ለመስጠት ተችሏል፡፡
- በ 1 ከተማ ላይ ማለትም አሶሳ ከተማ የሃብት አስተዳደር ዕቅድ (AMP) በማዘጋጀት 95 በመቶ ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን በተጨማሪም የመዋዕለ ንዋይ እቅድ /CIP/ በማዘጋጀት 82% እንዲተገበር ተደርጓል፡፡
- በከተሞች ፕላን ዝግጅት ወቅት የህዝብ ተሳትፎ እንዲያደረግና በፕላን ዝግጅት ወቅት 1200 350 ህዝብ እንዲሳተፍ ተደርጓል፡፡
- በቢሮው ውስጥ የሚገኙትን የኦዲት ግኝት ተሰብሳቢ ሂሳብና ተከፋይ ሂሳቦች አመላለስ ክትትል የማድረግ ስራ በመስራት 1788 ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡

## የበጀት አጠቃቀምና አያያዝ ስርዓት ከማሻሻለ አኳያ፡-

- በበጀት ዓመቱ ለቢሮው ከመንግስትና ከተለያዩ ምንጮች የሚመደበውን የመደበኛና የካፒታል በጀት በአግባቡ በመጠቀም ለታቀደለት ስራ የማዋል ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡
- በተጨማሪም የምግብ ዋስትና ፕሮግራምን ለማስኬድ ከመንግስትና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የሚመደበውን በጀት ለታቀደለት ስራ ከማዋል አንፃር ለቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚዎች 1,307,880 ብር ለመክፈል ተችሏል፡፡

## የበጀት አጠቃቀምን/አፈፃፀምን/ በተመለከተ

| የወጪ ዓይነት | የተስተካከለ በጀት | ሥራ ላይ የዋለ | ሸፋን በመቶኛ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| ደሞዝ | 9,753,054.00 | 4,614,723.56 | 47.32% | |
| ስራ ማስኬጃ | 3,327,785.00 | 2,095,014.95 | 63% | |
| ድምር | 13,080,839.00 | 6,709,738.51 | 51% | |
| ካፒታል | | | | |
| ለአሶሳ ከተማ መሰረተ ልማት ግንባታ ማቺንግ ፈንድ | 3,000,000.00 | 3,000,000.00 | 100% | |
| የክልል ም/ቤት እና መስተዳድር ም/ቤት ህንጻ ዲዛይን ግንባታ | 30,000,000.00 | 10,127,303.97 | 34% | |
| በሊዝ ለሚተላለፍ ቦታዎች ለኢንዱስትሪ ዞን | 1,000,000.00 | 4,040.00 | 0.40% | |
| አሶሳ ከተማ አስፖልት ጥገና እና ግንባታ | 10,000,000.00 | 639,492.46 | 6.39% | |
| የአሶሳ ከተማ የመንግስት ቁጠባ ቤቶች | 500,000.00 | 72,393.51 | 14.48% | |
| የአሶሳ ከተማ መዋቅራዊ ፕላን ክለሳ | 2,169,583.00 | 2,169,583.34 | 100% | |
| የከተማ ፕላንና መሬት አስተዳደር ስርዓት ግንባታ | 500,000.00 | 146,316 | 29% | |
| UIIDP | 604,313.00 | 537,124 | 89% | |
| ድምር | 60,250,422.00 | 22,868,867.48 | 47% | |

## የከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ማሳደግን ስንመለከት፡-

- በከተሞች በሊዝ የሚተላለፍ ቦታ በአገልግሎት አይነት ለይቶ ለማዘጋጀትና ለማስተላለፍ በከተሞች ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል 8.2 ሄክታር መሬት በማዘጋጀት 5.91 ሄክታር በምደባና 0.734 ሄክታር በጨረታ ለማስተላለፍ ተችሏል፡፡
- በክልሉ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፍ ሚሰማሩ ባለሃብቶች ቦታ በምደባ ከመስጠት አኳያ ለ57 ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት መሬት በመስጠት በ57 የኢንቨስትመንት ቦታዎች ላይ በውላቸው መሰረት መሰራታቸውን ክትትል ለማድረግ ተችሏል፡፡
- ለ2 ከተሞች ማለትም ለበርበርና ለዶቢ ከተሞች የሊዝ ዋጋ ክለሳና የቦታ ደረጃ የሚያሳይ ካርታ ለማዘጋጀት ተችሏል፡፡

## የከተማ ጽዳትና ዉበት አረንጓዴ ልማት አገልግሎት ማሻሻል በተመለከተ፡-

- በ2 ከተሞች ማለትም በባምባሲና በማንቡክ ከተሞች የደረቅ ቆሻሻ የማስወገጃ ቦታዎች እንዲዘጋጁ የተደረገ ሲሆን በ2 ከተሞች በአረንጓዴ መሰረተ-ልማትና በተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራዎች ዙሪያ በ3 ከተሞች ላይ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ተችሏል።

## በከተሞች የመልካም አስተዳደር ስርዓትን ከማሻሻል አንጻር፡-

- ያልተማከለ አስተዳደር ሥርአትን ለማጠናከር እውቅና የተሰጣቸው የገጠር የአገልግሎት መስጫ ማዕከላት በ3 የገጠር የአገልግሎት መስጫ ማዕከላት ማለትም ሆራዛብ፣ ኡንዱሉ እና ጎደሬ ላይ ማ/ቤት እንዲቋቋምላቸው ተደርጓል፡፡

## የከተማ ፕላን ዝግጅትና ትግበራን ማሳደግ ስንመለከት፡-

- በከተሞች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ልማት የሚያበረታታ ፕላን ከማዘጋጀት አኳያ 3 (75%) መሰረታዊ ካርታ (ኦዳ ቢልዲጊልዱ፣ ኡንዱሉና ሆራሀዛብ)፣ 3(74%) መሰረታዊ ፕላን (ኦዳ ቢልዲጊልዱ፣ ኡንዱሉና ሆራሀዛብ) እና 3(100%) የሠፈር ፕላን( NDP) በአሶሳ ከተማ ማዘጋጀት የተቻለ ሲሆን በተጨማሪም 3(100%) የመሠረተ-ልማት ቅንጅት ፕላን ለማዘጋጀት ተችሏል፡፡
- በ2 (100%) ከተሞች (ኡንድሉና ሆራሀዛብ) የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት እቅድ ለማዘጋጀተና ለመገምገም ተችሏል፡፡
- የፕላን አፈፃፀም ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ በ4 (50%) ከተሞች (በኦዳ፣ በአሶሳ፣ በመንጌና በባምባሲ) የመሬት አጠቃቀም አፈፃፀም ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ በዲዛ 119 ብሎክ፣ በሆሞሻ 50 ብሎክ፣ በባምባሲ 2 ብሎክ፣ በኡንድሉ 58 ብሎክና በመንጌ 32 ብሎክ በድምሩ 261 (100%) ሄክታር ብሎክ ለመክፈት የተቻለ ሲሆን 30 ለሚሆኑ ተነሺዎች የቦታ ሽንሽና ተደርጓል፡፡

## በከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትናን ማረጋገጥን በተመለከተ፡-

- በከተማ ልማት ስራዎች የስራ ዕድልን በመፍጠርና የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ከማጎልበት በግማሽ ዓመቱ በኮንስትራክሽን ለ75 ሴቶችና ለ185 ወጣቶች በድምሩ ለ260 ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የስራ ዕድል በመፍጠር የ1.3917 ሚሊዮን ብር የገበያ ትስስር ለመፍጠር ተችሏል፡፡
- በከተሞች በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ለ150 (50% ሴቶች ባማከለ መልኩ) ዜጎችን በዘርፉ ተጠቃሚ ለማድረግ ተችሏል፡፡
- የዜጎችን የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ ጋር በተያያዘ በከተሞች የሚገኙ የመስራት አቅም የሌላቸውና ለማህበራዊ ችግር የተጋለጡ የህብረተሰብ ክፍል የመሰረታዊና የማህበራዊ አገልግሎት እንዲያገኙ ከማድረግ አኳያ 600 ዜጎች የቀጥታ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ተችሏል፡፡
- የምግብ ዋስትና(UPSNP) ተጠቃሚ ከተሞችን 2 ለማድረስ ታቅዶ በዕቅዱ መሠረት ሁለት ከተሞችን ተጠቃሚ ለማድረግ ተችሏል፡፡

## የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ተወዳዳሪነትን ማሳደግ በተመለከተ፡-

- የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ተወዳዳሪነት ከማሳደግ ብቃት ያላቸውን የኮንስትራክሽን ዘርፍ ተዋናዮችን መፍጠር ወሳኝ ጉዳይ ነዉ፡፡ ከዚህም አንጻር በግማሽ ዓመቱ የኮንስትራክሽን ባለሙያዎች፣ የስራ ተቋራጮች፣ የአማካሪ ድርጅቶች፣ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎችና የግብዓት አቅራቢዎች ከመመዝገብ አኳያ 168(100%) የስራ ተቋራጮችን፣ 2(100%) አማካሪ ድርጅቶችን እንዲሁም 70(100%) የኮንስትራክሽን ባለሙያዎችን ለመመዝገብ ተችሏል፡፡
- ለ10 ባለሙያዎችና ለ2 የስራ ተቋራጮች ኢንስፔክሽን ስራ ተከናውኗል፡፡

## የተቀናጀ የጥራት ደረጃቸውን የጠበቀ የመሠረተ-ልማት አቅርቦትና ተደራሽነትን ማስፋፋት ስንመለከት፡-

- በከተሞች ማህበራዊ ደህንነትን መሰረት ያደረገ፣ ደረጃውን የጠበቀ፣ ጊዜና ወጪ ቆጣቢ፣ የተቀናጀ መሠረተ-ልማት አቅርቦት መርህን መሰረት ያደረገ መሰረተ-ልማት አውታሮች ግንባታ እና ጥገና ከማድረግ አንፃር 0.5 ኪ.ሜ ኮብል ስቶንና 1.43 ኪ.ሜ ጎርፍ ማስወገጃ /ዲች/ በአሶሳ ከተማ ለመገንባት ተችሏል፡፡

## ተደራሽና ደረጃውን የጠበቀ የቤት አቅርቦትን በተመለከተ ፡-

- በክልሉ ከተሞች ከሚታዩ ችግሮች መካከል ተደራሽ እንዲሁም ደረጃቸውን የጠበቁ ቤቶች እንዲገነቡ ከማድረግ ውስንነት መኖሩ ነው፡፡ በግማሽ ዓመቱም ይህንን ችግር ከመፍታት 600 ቤቶችን

በማህበራት እንዲሁም 100 ደረጃቸውን የጠበቁ ቤቶችን በግለሰቦች እንዲገነቡ የታቀደ ሲሆን በማህበራት 6(1%) እንዲሁም በግለሰቦች 403(100%) የተለያዩ አይነት ያላቸው ቤቶች መገንባት ተችሏል፡፡

- ለሚገነቡ የመኖሪያ ቤቶች እንደየ ከተሞቹ ሁኔታ 5 የተለያዩ አዳዲስና የማሻሻያ ስታንዳርድ ዲዛይኖች ከክልሉ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማጣጣም ለማዘጋጀት ታቅዶ በዕቅዱ መሠረት ለማዘጋጀት ተችሏል፡፡

### የህንጻ ግንባታ አስተዳደር ስርዓትን ከማሻሻል አንጻር፡-

- የህንጻ ግንባታውንና አስተዳደር ስርዓትን ከማሻሻል በግማሽ ዓመቱ በሚገነቡ በ18 (100%) የመንግስት ህንፃዎች (ኩርሙክ /ዱሽታሎ/፣ አሶሳ /ጉንባ/፣ ከማሽ ከተማ አስተዳደርና መተከል ዞን) ላይ ክትትልና ቁጥጥር ስራ ለመስራት ተችሏል፡፡
- በከተሞች ለሚገኙ 3 ቁጠባ ቤቶች ጥገና ለማድረግ ተችሏል፡፡
- በዕቅድ ዘመኑ 1 መለስተኛና 1 ከፍተኛ ሕንጻ የተቋራጮችን በማሳተፍ የመንግስት ህንጻዎች በጥራት እንዲገነቡ ለማድረግ ተችሏል፡፡
- ለገጠር የልማት ማዕከላት እንደየ አካባቢው የአየር ሁኔታና አሰፋፈር ጋር የተጣጣሙ 3 ዲዛይኖችን ለመከለስ ታቅዶ በዕቅዱ መሠረት ለመከለስ ተችሏል፡፡
- በክልሉ 77 ነባር የመንግስት ህንጻዎች እንዲሁም 2 አዲስ የግንባታ ፕሮጀክቶች መዝገባ ተከንውኗል፡፡
- የጥገና አገልግሎት የሚያስፈልጋቸው ህንጻዎች እንዲጠገኑ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመወያየት ሃሳብ በማቅረብ የህንፃ ሀብቶችን የመንከባከብ፣ የመጠበቅና በጥንቃቄ የመጠቀም ልምድን የማዳበር ስራዎችን በመሪነት እንዲከናወኑ ለማድረግ ታቅዶ በሩብ ዓመቱ የጥገና አገልግሎት የሚያስፈልጋቸው 61 (100%) ነባር የመንግስት ህንፃዎች /211 ቤቶች/ የመለየት ስራ ተሰርቷል፡፡
- በክልሉ በጀት ለሚሰሩ ለ18 አዲስ ግንባታ ድዛይንና የስራ መዘርዝር በማዘጋጀት በ3 ፕሮጀክቶች ላይ የኢንስፔክሽን ስራ ለማካሄድ ተችሏል፡፡
- የህንጻ አዋጁ ተፈጻሚ በሚሆንባቸው ከተሞች የሚገነቡ 514 ህንጻዎች የግንባታ ፍቃድ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

### የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም ማሳደግ በተመለከተ፡-

- የተቋሙን የስልጠና ፍላጎት በመለየት በልዩ ልዩ የአመራር ጥበብ የአገር ውስጥ የአጫጭር ጊዜ ስልጠና እና ለተቋሙ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ላይ ለዘርፉ 6 አመራሮች ስልጠና እንዲያገኙ ለማድረግ ተችሏል፡፡
- በ3 ከተሞች የማዘጋጃ ቤታዊ የአገልግሎት ስታንዳርዳይዘሽንና የአፈፃፀም ምዘና ዘርፍ እንዲጠናከርና እንዲደራጅ በማድረግ የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዶች እንዲተገበሩና የአገልግሎት አሰጣጥ እንዲሻሻል ለማድረግ ታቅዶ ከዕቅድ በላይ በ6 ከተሞች ስታንዳርዱን ለመተግበር ተችሏል፡፡
- የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት የሙያ መስኮች 5 መሪ መዛኖች የማንቅያ ስልጠና እንዲያገኙ ለማድረግ ተችሏል፡፡
- ከተሞች ገቢያቸውን የማሳደግና የማስተዳደር አቅማቸውን ለማረጋገጥ ለ60 ባለሙያዎች ስልጠና ለመስጠት ተችሏል፡፡
- የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ስታንዳርዶች እንዲተገበሩ፤ የዜጎች ቻርተር እንዲዘጋጅና ለዜጎች ተደራሽ እንዲሆን፤ የአገልግሎት አቅርቦቱም እንዲሻሻል በማድረግ፤ በአገልግሎት አቅርቦት ማሻሻያ ዙሪያም የልምድ ልውውጥ መድረኮችን ለማዘጋጀት እንዲረዳ በ2 ከተሞች ላይ በአገልግሎት አሠጣጥ ዙሪያ ክትትል ለማድረግ ተችሏል፡፡

❖ የመንግስት ህንጻ ግንባታ አፈጻጸም ለማሳደግ ለ22 የጥቃቅን አነስተኛና መለስተኛ ኢንተርፕራይዞች ስልጠና ለመስጠት ተችሏል፡፡
❖ በቤቶች ልማት ዘርፍ የተሰማሩ 8 የዘርፉ ሠራተኞች ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

**የዘመናዊ ቴክኖሎጂ አቅርቦት እና መረጃ ስራ አመራር ማሻሻል**

❖ የከተሞች ገቢ አሰባሰብ ስታቲክስ፣ የመሰረተ-ልማት መረጃ፣ የከተሞች የህዝብ ተሳትፎ ስታቲክስ፣ የከተሞች የሰው ሀይል ፕሮፋይል መረጃና የከተሞች የሶሾ ኢኮኖሚ ጥናት መረጃ 91 በመቶ ተደራጅቶ እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡
❖ የኮንስትራክሽን ግብአቶች ወቅታዊ ዋጋ (Standard Price Index) ለማደራጀት ታቅዶ በዕቅዱ መሠረት ለማደራጀት ተችሏል፡፡
❖ በቢሮው የመረጃ መረብ ደህንነትና ፍሰት መቶ በመቶ ክትትል በማድረግ ወቅታዊ የመጠባበቂያ ቅጂ/Back up/ የመውሰድ ስራዎችን ለማከናወን ታቅዶ በዕቅዱ መሠረት ለማከናወን ተችሏል፡፡
❖ በከተሞች ያሉ ስራ ፈት፣ ስራ አጥና በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ዜጎች መረጃ ለማደራጀት ታቅዶ በዕቅዱ መሠረት ለማደራጀት ተችሏል፡፡

በአጠቃለይ በዘርፉ በ2013 በጀት ዓመት በግማሽ ዓመቱ የተጣሉ ግቦችን ለማስፈጸም በየእርከኑ በሚገኙ አመራሮችና ፈጻሚዎች ርብርብ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ በግማሽ ዓመቱ በተሰሩ ስራዎች አንፃር የግቦች አፈፃፀም ስንመለከት በይበልጥ በጣም ዝቅተኛና በዝቅተኛ ደረጃ ላይ መሆናቸውን ያሳያል፡፡ ሲለሆነም በግማሽ ዓመቱ የተሻለ አፈፃፀም የተመዘገቡባቸው ግቦች እንዳሉ ሁነው በዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ በሆኑ የአፈፃፀም ደረጃ ያሉት ግቦች ደግሞ ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ናቸው፡፡ በመሆኑም በሚቀጥሉት ቀሪ በጀት አመት አሁን የታየውን ዝቀተኛ የግብ አፈጻጸሞችን ለማካካስ በተሻለ የስራ ፍላጎትና ቁርጠኝነት መስራት ያስፈልጋል፡፡

የኮቪድ 19 መረጃዎች

➢ የሁለት አዋቂ እርምጃ ያህል ርቀታችንን እንጠብቅ!!
➢ እጃችንን በየጊዜው ለ20 ሰከንድ እንታጠብ/ከአልኮል የተዘጋጁ ማጽጃ/ሳኒታይዘር/ በመጠቀም የእጅዎን ንጽህና ይጠብቁ!!
➢ በሚያስሉበትና በሚያስነጥሱበት ወቅት በሶፍት ወይም ክንዲዎን በማጠፍ አፍና አፍንጫዎን ይሸፍኑ!!
➢ ባልታጠበ እጃችን አፍ፣ አፍንጫችንና አይናችንን አንንካ!!
➢ በማንኛውም ቦታ ላይ ማክስ ሳያደረጉ አይንቀሳቀሱ!!

ውድ አንባቢዎቻችን የእናንተ ገንቢ አስተያየት ለስራችን ወሳኝ በመሆኑ በዜና-መጽሄታችን ላይ ያላችሁን አስተያየት ብታደርሱን በደስታ እንቀበላለን!!


አዘጋጅ ፡- የቢሮው ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት

ስልክ 0577751802

ኢሜይል bgrs udcb@.gmail.Com

ፌስቡክ BGRS- Urban Development and Constraction Bureau


ጥር 2013